

ይህ ሥዕል ብፁዕ አቡነ ባስልዮስ በእስክንድርያው ሊቀ ጳጳሳት በአቡነ ዮሳብ እጅ ተቀብተው ሊቀ ጳጳሳት ዘኢትዮጵያ ተብለው ሲሾሙ ግብፃውያንና ኢትዮጵያውያን ጳጳሳት በሥራው ተካፋዮች ሆነው ይታያሉ ይህ የግብፅንና የኢትዮጵያን ጳጳሳት አንድነት ያሳያል ።



ይህ ሥዕል የኢትዮጵያን ሲኖዶስ አባላት ሥዕል ያሳያል ፤ እነሱም በመካከል ያሉት ብፁዕ አቡነ ባስልዮስ ርእሰ ሊቃነ ጳጳሳት ወፓትርያርክ ዘኢትዮጵያ ያሉት ብፁዕ አቡነ ቴዎፍሎስ ዘሐረር ፤ ብፁዕ አቡነ ጢሞቴዎስ ዘሲዳሞ ናቸው ።

በስተግራ ብፁዕ አቡነ ያዕቆብ ዘትግሬ ፤ ብፁዕ አቡነ ይስሐቅ ዘወለጋ ናቸው ።

እሊህም አቡነ ያዕቆብ በእስክንድርያው ሊቀ ጳጳስ በአቡነ ዮሳብ ዘንድ በእስክንድርያ ተቀብተው የተሾሙ ናቸው ።

በኋላ የሚታዩት ደግሞ አቡነ ማቴዎስ ዘጎጃም ፥ አቡነ ፊልጶስ ዘኢየሩሳሌም ፥ አቡነ ማርቆስ ዘኤርትራ አቡነ ታዴዎስ ዘኢሉባቦር ፥ አቡነ ገብርኤል ዘወሎ ናቸው ።

እሊህም በኢትዮጵያዊው ፓትርያርክ በአቡነ ባስልዮስ ተቀብተው የተሾሙ ናቸው ።



ይህ ሥዕል ንግሥተ ዐዜብ የሰሎሞንን ዜና መንግሥት ሰምታ ለመጎብኘት በሔደች ጊዜ ማንም ያስተማራት ሳይኖር በሕገ ልቡና እውቀት በእስራኤል ዙፋን ላይ ሊያነግሥህ የወደደ እግዚአብሔር ይክበር ይመስገን ብላ እንደ አመሰገነች ያሳያል ነገ ቀዳ፤፲፥፱ ።



ይህ ሥዕል በአብርሃ ወአጽብሐ ዘመነ መንግሥት ክርስትና ወደ ኢትዮጵያ ያመጣውን ፍሬ ምናጦስን ወይም ከሣቴ ብርሃን ሰላማን ያመለክታል ።



ይህ ሥዕል እግዚአብሔር ለዳዊት መንግሥትህን ከዘርኽ አላወጣውም ብሎ በማለለት መሠረት ከቀዳማዊ ምኒልክ ዘርዕ ሳይቋረጥ ወርዶ አሁን ባለንበት በሃያኛው ዘመን ግርማዊ ቀዳማዊ ኃይለ ሥላሴ ከቀደምቶቻቸው ከአብርሃ ወአጽብሐ ሲያያዝ በወረደው ሥርዓት ተቀብተው እንደ ነገሡ ያሳያል ሕገ መን ቍ ፪ ተመልከት ።



ይህ ሥዕል ከኢትዮጵያ ዕጨጌዎች ፻፲ኛውን ዕጨጌ ገብረ ጊዮርጊስን ያሳያል ።
አሁን ፓትሪያርክ ዘኢትዮጵያ ።

እንግዲህ ፡ እርስዎ ፡ እንዲህ ፡ ብሎ ፡ ለመናገር ፡ የደፈሩበት ፡ የኢትዮጵያ ፡ ቤተ ፡ ክርስቲያን ፡ እንደ ፡ አይሁድ ፡ ልማድ ፡ ደም ፡ ስታፈስ ፡ ስብ ፡ ስታጤስ ፡ ወይም ፡ ላም ፡ በግ ፡ [illegible] ፡ የላም ፡ የፍየል ፡ ደም ፡ በሐር ፡ ጉንጉን ፡ በጽሕመ ፡ ጠሊ ፡ ስትረጭ ፡ አይተዋልን ፡ ወይስ ፡ ጠላት ፡ ይቀባል ፡ ጥላት ፡ እንደሚባለው ፡ ስሟን ፡ ላጥፋ ፡ ብለው ፡ ከልብዎ ፡ አንቅተው ፡ ይዋሹ ፡ ያዩት ፡ ነገር ፡ ካለ ገልጸው ፡ ይጻፉና ፡ እኔም ፡ የሚገባ ፡ መልሱን ፡ እሰጥዎታለሁ ።

፬/ በዚሁ ፡ በመሰየቷ ፡ ዘመናት ፡ ብዙ ፡ ስሕተቶችና ፡ መልካም ፡ ኑሮን ፡ መንፈሳዊ ፡ አስተዳደርን ፡ የሚያበላሹ ፡ ቁሀሎች ፡ ገፀባት ፡ ከሮማ ፡ ቤተ ፡ ክርስቲያንም ፡ የለይዋት ፡ እነዚህ ፡ ስሕተቶች ፡ ሳይኾኑ ፡ አይቀሩም ፡ ብለዋል ።

፮ኛ ኢትዮጵያን ፡ ከሮማ ፡ የለያት ፡ በሮማ ፡ ቤተ ፡ ክርስቲያን ፡ ላይ ፡ የሚታየው ፡ ስሕተት ፡ ነው ፡ እንጂ ፡ ሌላ ፡ አይደለም ። ከሮማ ፡ መለየቷስ ፡ በሮማ ፡ ቤተ ፡ ክርስቲያን ፡ ከሚነገረው ፡ ስሕተት ፡ ጠበቃት ፡ እንጂ ፡ የጎዳት ፡ ነገር ፡ የለም ።



ይህ ሥዕል ክርስቶስ በሥጋ እንደ ተነሣ ያሳያል ማቴ ፳፰ ፩—፮ ።

